# ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የመኖሪያ ቤት መሠረታዊ መረጃዎች በጨረፍታ

የU.S. Department of Housing and Urban Development (HUD፣ የዩናይትድ ስቴትስ የመኖሪያ ቤት እና የከተማ ልማት መምሪያ) በአጠቃላይ ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መኖሪያ ቤት ብሎ የሚገልጸው፣ አንድ ቤተሰብ የውኃ እና መብራት ክፍያዎችን እንዲሁም የቤት ኪራይ/የቤት መግዣ ብድርን ጨምሮ ለመኖሪያ ቤት ወጪዎች ከጠቅላላ ወርሃዊ ገቢው ከ30% ያልበለጠ ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች እስከ 40% የሚከፍል ሲሆን ነው።



## ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት ዓይነቶች

**Mobile Section 8/Tenant Based Voucher (ተንቀሳቃሽ የሴክሽን 8/በተከራይ ላይ የተመሠረተ ቫውቸር)**

ይህ ድጎማ ከተከራዩ ጋር አብሮ የሚቀጥል ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ በየትኛውም የUnited States (ዩናይትድ ስቴትስ) ግዛት ውስጥ ሊያገለግል ይችላል። የቫውቸር ባለቤቱ የራሱን መኖሪያ ቤት የሚፈልግ ሲሆን፣ ቤቱም በቤቶች ባለሥልጣን/ኤጀንሲ መጽደቅ ይኖርበታል።

**Site Based Housing/Public Housing (በሳይት ላይ የተመሠረቱ መኖሪያ ቤቶች/የሕዝብ መኖሪያ ቤቶች)**

በሕንጻው ወይም በልማቱ ውስጥ ያሉት ሁሉም ክፍሎች የገንዘብ ድጎማ የሚደረግላቸው ናቸው። ተከራዩ መኖሪያ ክፍሉን የሚለቅ ከሆነ የገንዘብ ድጎማው ተከራዩ ቀጣይ ወደሚሄድበት መኖሪያ አይተላለፍም።

**Project Based Housing (በፕሮጀክት ላይ የተመሠረቱ መኖሪያ ቤቶች)**

በሕንጻ ውስጥ ያሉ የተወሰኑ ክፍሎች የገንዘብ ድጎማ የሚደረግላቸው ቢሆንም፣ ሙሉ ሕንጻው ግን ድጎማ ስለማይደረግለት ተከራዩ የመኖሪያ ቦታውን የሚቀይር ከሆነ የገንዘብ ድጎማው ይቆማል።

**Massachusetts Rental Voucher Program (MRVP፣ የMassachusetts የኪራይ ቫውቸር ፕሮግራም)**

እነዚህ ድጎማዎች ተንቀሳቃሽ/በተከራይ ላይ የተመሠረቱ ወይም በፕሮጀክት ላይ የተመሠረቱ ሊሆኑ ይችላሉ። ተንቀሳቃሽ ቫውቸሮች የሚያገለግሉት MA ግዛት ውስጥ ብቻ ነው።

**የገቢ ገደብ የተጣለባቸው ቤቶች**

አመልካቹ ዝቅተኛ እና ከፍተኛ የገቢ መመሪያዎችን ማሟላት ይኖርበታል።

## ማን

**የቤቶች ባለሥልጣናት**

አብዛኞቹ በMA ውስጥ የሚገኙ ከተሞች የቤቶች ባለሥልጣን አሏቸው። የቤቶች ባለሥልጣናት ለቫውቸሮች እና ለሕዝብ መኖሪያ ቤት የሚሆን የገንዘብ ድጋፍን ከፌዴራል እና ከክልል መንግሥታት ያገኛሉ። የቤቶች ባለሥልጣናት የቫውቸር ስርጭትን የሚቆጣጠሩ ሲሆን፣ በፕሮጀክት ላይ ለተመሠረቱ ቤቶች የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት ኣና የሕዝብ ወይም በሳይት ላይ የተመሠረቱ መኖሪያ ቤቶችን ገንብተው ይንከባከባሉ።

**የቤቶች ኤጀንሲዎች**

Regional Administering Agencies (የክልል አስተዳዳሪ ኤጀንሲዎች) የተለያዩ የቤት ኪራይ ድጎማ ፕሮግራሞችን የሚያስተዳድሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ተቋማት ናቸው። በተጨማሪም Residential Assistance for Families in Transition (RAFT፣ ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ቤተሰቦች የመኖሪያ ቤት ድጋፍ) የተሰኘውን የክልሉን የገንዘብ እርዳታ ፕሮግራም የሚያስተዳድሩ ሲሆን፣ ሌሎች አገልግሎቶችንም ይሰጣሉ። Metro Housing|Boston ለCambridge ነዋሪዎች አገልግሎት የሚሰጠው ክልላዊ ኤጀንሲ ነው።

**Cambridge Housing Department (የCambridge የመኖሪያ ቤቶች መምሪያ)**

ይህ የCambridge ከተማ አስተዳደር መምሪያ በተለያዩ ፕሮግራሞች አማካኝነት ዝቅተኛ፣ መካከለኛ እና መካከለኛ-ከፍተኛ ገቢ ላላቸው አባውራዎች ተመጣጣኝ የኪራይ እና የቤት ባለቤትነት እድሎችን ያቀርባል።

## ድጎማ ለሚሰጣቸው የመኖሪያ ቤቶች ማመልከት

የፌዴራል እና የክልል ድጎማ የሚደረግላቸው መኖሪያ ቤቶች። በአጠቃላይ አንድ አመልካች የሚያገኘው ገቢ ከአካባቢው አማካይ ገቢ (AMI) 50% ወይም ከዚያ በታች መሆን ይኖርበታል። አንዳንድ ፕሮግራሞች የአንድ አመልካች ገቢ እስከ 80% AMI ወይም ከዚያ በታች እንዲሆን ይፈቅዳሉ። አመልካቾች ምንም ዓይነት ገቢ ባይኖራቸውም እንኳ ማመልከት ይችላሉ።

ነዋሪዎች በCambridge እና በአካባቢው ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው መኖሪያ ቤት ሲፈልጉ ሊያሟሏቸው የሚገቡ 3 ዋና ዋና ማመልከቻዎች አሉ።

**1. Cambridge Housing Authority (CHA፣ የCambridge የመኖሪያ ቤቶች ባለሥልጣን)**
በቀጥታ ለCHA በማመልከት ተንቀሳቃሽ የሴክሽን 8 ቫውቸር እንዲሁም በCambridge ያሉ የመኖሪያ ቦታዎችን እና በፕሮጀክት ላይ የተመሠረቱ ቤቶችን ማግኘት ይችላሉ። **https://cambridge-housing.org/applicants**

**2. CHAMP (Common Housing Application for Massachusetts Programs፣ ለMassachusetts ፕሮግራሞች የጋራ የቤት ማመልከቻ)**
በMA ግዛት ለሚደገፉ የሕዝብ መኖሪያ ቤቶች በሙሉ የቀረበ ሁሉንም ያማከለ ማመልከቻ። **Camb.ma/CHAMP**

**3. Centralized Section 8 Application (ሁሉንም ያማከለ የሴክሽን 8 ማመልከቻ)**
በመላ ግዛቱ ለሚገኙ ለአብዛኞቹ የቤቶች ባለሥልጣናት የሚላክ አንድ ወጥ ማመልከቻ። ይህ ማመልከቻ ለCambridge ስለማይሠራ በቀጥታ ለCHA ማመልከት አለብዎት። **http://www.section8listmass.org/**

## የተገደበ ገቢ ላላቸው መኖሪያ ቤቶች ማመልከት

ብዙውን ጊዜ የኪራይ መጠኑ ከገበያ ዋጋ ያነሰ ነው። አንዳንድ ፕሮግራሞች ኪራዩን ሊቀንሱ ቢችሉም፣ ሌሎቹ ግን መቀነስ አይችሉም።

*Cambridge Housing Department*

**1. የኪራይ አመልካቾች ስብስብ**
Inclusionary Rental Program (ሁሉንም የሚያካትት የኪራይ ፕሮግራም) (ከ50-80% AMI ላላቸው ቤተሰቦች) እና Middle-Income Rental Program (ለመካከለኛ-ገቢ የሚሆን የኪራይ ፕሮግራም) (ከ80-120% AMI ላላቸው ቤተሰቦች) የሚያገለግል አንድ ወጥ ማመልከቻ። **https://www.cambridgema.gov/CDD/housing/forapplicants/rentalapplicantpool**

**2. ለመጀመሪያ-ጊዜ መኖሪያ ቤት ለሚገዙ ሰዎች የቀረቡ ዕድሎች**
Homebuying Lotteries (የቤት ግዢ ዕጣዎችን)፣ HomeBridge (ሆምብሪጅን) እና Homeownership Resale Pool (ዳግም የሚሸጡ ቤቶችን ለመግዛት የተመዘገቡ አመልካቾች ስብስብ) የሚመለከቱ የማመልከቻ መረጃዎች። **https://www.cambridgema.gov/CDD/housing/forhomebuyers**

*የገቢ ገደብ ከተጣለባቸው ቤቶች ጋር የተያያዙ ሌሎች ዕድሎች*

**3. Housing Lotteries and Low-Income Housing Tax Credit Units (የቤት ዕጣዎች እና ዝቅተኛ-ገቢ ላላቸው ሰዎች የሚዘጋጁ በታክስ ድጋፍ የሚገነቡ ቤቶች)**
እንደ ቤቶች መገኘት ሁኔታ ይወሰናል። **https://search.housingnavigatorma.org/**



# ማጠቃለያ

የቤት ማመልከቻን የመሙላት ሂደት ግራ የሚያጋባ እና ከአቅም በላይ ሊሆን ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ የOffice of the Housing Liaisonን (የቤት ግንኙነት ቢሮን) በዚህ ኢሜይል አግኝተው ያነጋግሩ፡- housingliaison@cambridgema.gov